በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FINANCE

# በልማት አጋሮች ድጋፍ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የውሎ አበልና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች የአከፋፈል መመሪያ ቁጥር 1045/2017

የካቲት 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

ሀገራችን በአስር አመቱ መሪ የልማት ዕቅድ የተቀመጡ የልማት ግቦችን ለማሳካት ለፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚጠይቀውን ግዙፍ መዋለ-ንዋይ ለማሟላት የሀገር ውስጥ ጥሪትን አሟጦ ከመጠቀም ባሻገር ከልማት አጋሮች የውጭ ሀብት በማሰባሰብና ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ በማድረግ የተለያዩ የረጅምና የአጭር ጊዜ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ መንግስት ከልማት አጋሮች ጋር ጠንካራ የኢኮኖሚ ትብብር በመመስረቱ የሀገሪቱን የልማት ዕቅዶች ለማሳካት በተለያዩ መስኮች ድጋፍ እየተገኘ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ አለማቀፍ የኢኮኖሚ ትብብር ሀገራችን በቀጣይ ዓመታት የኢኮኖሚ ዕድገት እንድታስመዘግብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት ሀገራችን ያስመዘገበችውን ሁለገብ ዕድገት ለማስቀጠልና የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሁለተኛው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም ተቀርጾ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት የተቀረፁ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ ከሀገር ውስጥ ሀብት በተጨማሪ ከልማት አጋሮች የሚገኘው የውጪ ሀብት ትርጉም ያለው ድርሻ እንደሚይዝ ይታወቃል፡፡

ከልማት አጋሮች በብድርና እርዳታ መልክ የሚገኘው ሀብት በኢኮኖሚው ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን፣ ዘላቂ የልማትና የማህበራዊ አገልግሎት ፕሮግራሞችን እንዲሁም ለዜጎች መሠረታዊ ከለላ ትርጉም ያለው ጠቀሜታ የሚሰጡ እንደ ውሃ፣ ትምህርት፣ ጤና፣ የምግብ ዋስትና እና የመሳሰሉ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ ለየሚውል በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

የልማት አጋሮች የሚሰጡት የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ በትክክል ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉና ተጨባጭ ውጤት ማምጣቱን ለማረጋገጥ በብድር ወይም በእርዳታ ስምምነቱ ውስጥ የአፈጻጸም መከታተያ salary መለኪያዎች ይካተታሉ፡፡

በዚህም ምክንያት በልማት አጋሮች ድጋፍ በመካሄድ ላይ የሚገኙ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው በጀት፣ ጊዜና ጥራት ተጠናቀው ለዘላቂ ሀገራዊ ልማት መፋጠን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ፣ ከፕሮጀክቶች ቀረፃ ጀምሮ፣ በትግበራ እና ክትትልና ግምገማ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መሥራት፣ የማህበረሰብን ተሳትፎ ማረጋገጥ፣ የክትትልና ግምገማ ሥራዎችን ማካሄድ እና ችግሮችን በወቅቱ መፍታት ለፕሮጀክቶች የተሳለጠ አፈጻጸም አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም ከትብብሩ የምታገኘውን የውጭ ሀብት እንዲጨምር በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

በ2008 ዓ.ም በልማት አጋሮች ድጋፍ ለሚካሄዱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሚያገለግል ወጥ የሆነ አማራጭ የውሎ አበል እና ተዛማጅ ወጪዎች አከፋፈል መመሪያ ተዘጋጅቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በሂደትም እያደገ ከመጣው የገበያ ዋጋ ጋር ለማጣጣም መመሪያው በ2011 እና 2013 ዓ.ም እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል እስካሁን በሥራ ላይ የቆየው የውሎ አበል ተመን በአሁኑ ወቅት ካለው የገበያ ዋጋ ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ እና በመስክ ክትትልና ግምገማ ሥራዎችም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደሩ እና የዋጋ ግሽበቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ እንዲሁም ይህን መመሪያ ከሚጠቀሙ ባለድርሻ አካላት ተደጋገሚ መመሪያው እንዲሻሻል ጥያቄዎች ሲቀርቡ ቆይተዋል፡፡

በመሆኑም የገንዘብ ሚንስቴር ይህን መነሻ በማድረግ ከሁሉም ክልሎች እና ከሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች መረጃዎችን በማሰባሰብ ጥናት ያከነወነ ሲሆን አሁን ካለው የአገልግሎትና የሸቀጦች ዋጋ አንጻር ተቀራራቢ የሆነ በልማት አጋሮች ድጋፍ በሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ለሚደረጉ ክንውኖች የሚያገለግል የውሎ አበል መመሪያ ተሻሽሏል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

## 1.1. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በልማት አጋሮች ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀት፣ ጊዜና ጥራት እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ከፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቀረፃ፣ ትግበራ እና ክትትልና ግምገማ ጋር በተያያዘ በሚደረጉ ክንውኖች ወቅት የሚያጋጥሙ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችል ወጥ የሆነ የውሎ አበልና ተዛማጅ ወጪዎች አከፋፈል ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

## 1.2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በልማት አጋሮች ድጋፍ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የውሎ አበልና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች የአከፋፈል መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 1.3. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፣

1.3.1 **የማህበረሰብ አባላት፡-** ማለት የመንግሥት ተቀጣሪ ወይም ተሿሚ ያልሆኑ በልማት አጋሮች ድጋፍ ከሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቀረፃ፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ ጋር በተያያዘ በአገር ውስጥ በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ህብረተሰብን ወክለው የሚሳተፉ ግለሰቦች ማለት ነው፡፡

1.3.2 **ሌሎች ባለድርሻ አካላት፡-** ማለት በልማት አጋሮች ድጋፍ ከሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ጋር በተያየዘ በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተጋበዙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበረሰብ እና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች ማለት ነው፡፡

1.3.3 **ተሳታፊ፡-** ማለት በልማት አጋሮች ድጋፍ በሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቀረጻ፣ አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ ጋር በተያያዘ በአገር ውስጥ በሚደረጉ ሥልጠናዎች፣ ዓውደ-ጥናቶች፣ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮች፣ ኮንፍረንሶች፣ የመስክ ክትትልና ግምገማዎች የማህበረሰብ-አቀፍ ንቅናቄዎች ላይ የሚሳተፉ እንዲሁም የማህበረሰብ ተሳትፎ ሥራዎችን የሚያዘጋጁ እና የሚያስተባብሩ ግለሰቦች ማለት ነው፡፡

1.3.4 **ውሎ አበል፡-** ማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ በተሰጠው ትርጉም መሠረት እንደ አግባብነቱ የቀን ውሎ አበልና የውሎ ገባ አበል ማለት ነው፡፡

1.3.5 **የልማት አጋሮች፡-** ማለት ለልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የፋይናንስና፣ የቴክኒክ እና የዓይነት ድጋፍ በብድር ወይም በዕርዳታ መልክ በመስጠት የመንግስትን የልማት አጀንዳ የሚደግፉ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት፣ መንግስታት፣ ቻሪቲዎችና ፋውንዴሽኖች ናቸው፡፡

1.3.6 **ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች፡-** በልማት አጋሮች ከሚደገፉ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቀረፃ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ክንውኖች ጋር በተያያዘ ከውሎ አበል ውጭ ያሉ የትራንስፖርት እና ከስራው ጋር አግባብነት ያላቸው ሌሎች ወጭዎች ማለት ነው፡፡

1.3.7 **በልማት አጋሮች ድጋፍ በሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ላይ የሚካሄዱ ክንውኖች ማለት**

በልማት አጋሮች ከሚደገፉ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቀረፃ፣ አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ ጋር በተያያዘ በፌዴራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ የሚካሄዱ ስብሰባዎች፣ ሥልጠናዎች፣ ዓውደ-ጥናቶች፣ ሴሚናሮች፣ ኮንፈረንሶች፣ የመስክ ጉብኝቶች፣ ክትትልና ግምገማዎች፣ የማህበረሰብ አቀፍ ንቅናቄና የጉልበት ሥራዎች ናቸው፡፡

1.3.8 **የመንግስት ተሿሚዎች**

የመንግስት ተሿሚ ማለት በቀድሞ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በነሀሴ 3/ 2005 ዓ.ም ስራ ላይ ባዋለው የተሿሚዎች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ ላይ በአንቀፅ ሶስት በተራ ቁጥር አንድ እና ሁለት ስር የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

1.3.9 **የተቋማት የስራ ሃላፊዎች**

የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ማለት በፌደራል፣ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ያሉ የመንግስት መ/ቤቶች የስራ ክፍል ሃላፊዎች ናቸው፡፡

1.3.10 **ሪጂዮፖሊሲ ከተማ**

ሪጂዮፖሊሲ ከተማ ማለት የከተማና ልማት ሚኒስቴር ነሐሴ 2015 ዓ.ም ባወጣው የከተሞች ፈርጅ መወሰኛ ስታንዳርድ መሰረት ከተሞች በመመሪያው ያሉ ስታንዳርዶችን አሟልተው ወደ ሪጂዮፓሊሲ ከተማነት ሲያድጉና ይህም በክልል ም/ቤት ሲፀድቅ ነው፡፡

## 1.4. አውጭው ባለስልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር የውጭ ሀብትን የማሰባሰብና የተሰበሰበው ሀብት በታለመለት መንገድ ተግባራዊ መሆኑን እንዲከታተል በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1.5. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በልማት አጋሮች ድጋፍ በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በፌደራልና በክልል በሚዘጋጁ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮች፤ ኮንፍረንሶች፤ ዓውደ-ጥናቶች፣ ስልጠናዎች፣ የመስክ ክትትልና ግምገማዎች፣ የማህበረሰብ-አቀፍ ንቅናቄዎች እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ስራዎች ሲዘጋጁ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የውሎ አበል

## 2.1 የውሎ አበል አከፋፈል

የውሎ አበል አከፋፈል በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የቀን ውሎ አበል ማሻሻያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 መሰረት ለቁርስ 10% ለምሳ 25%፣ ለእራት 25%፣ እንዲሁም ለመኝታ 40% በሚል ተከፋፍሎ የሚሰላ ይሆናል፡፡

## 2.2 ለውሎ አበል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

የመንግሥት ሠራተኛ እና/ወይም የሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ በልማት አጋሮች ድጋፍ ከሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የተለያዩ ክንውኖች ጋር በተያያዘ ለመስክ ሥራ ተሰማርቶ ዕለቱን ወደ መኖሪያው መመለስ ካልቻለ ለእያንዳንዱ በመስክ ሥራ ለቆየበት ቀን ወይም ቀኑን ሙሉ ከሥራ ቦታው ውጭ በመስክ ስራ ላይ አሳልፎ ዕለቱን ወደ መኖሪያው ከተመለሰ የምግብ ወጪውን ለመሸፈን አሁን በስራ ላይ ባለው የሲቪል ሰርቪስ የውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 2 እና 3 መሠረት የውሎ አበል ለማግኘት ብቁ ይሆናል፡፡

## 2.3 ለመንግስት ተሿሚዎች ተግባራዊ የሚሆን የውሎ አበል አከፋፈል

የመንግስት ተሿሚዎች በልማት አጋሮች ድጋፍ በሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ የውሎ አበል አከፋፈላቸው መንግሥት በልዩ ሁኔታ ባወጣው መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደ አማራጭ በዚህ መመሪያ በየደረጃው የተቀመጠውን የቀን ውሎ አበል መጠን መጠቀም ይቻላል፡፡

## 2.4 ለመንግስት ሠራተኞች ተግባራዊ የሚሆን የውሎ አበል አከፋፈል

2.4.1 የመንግሥት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በአዲስ አበባ ከተማ በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ በስራ ላይ ባለው የሲቪል ሰርቪስ የውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 2 እና 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ደመወዝን እና የሥራ ደረጃን መሠረት በማድረግ ልዩነት ሳይደረግ በቀን **ብር 1,500** የውሎ አበል ይከፈላል፡፡

2.4.2 የመንግሥት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በክልል፣ በዞን እና በሪጂዮፓሊሲ ከተሞች በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ አሁን በስራ ላይ ባለው የሲቪል ሰርቪስ የውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 2 እና 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ደመወዝን እና የሥራ ደረጃን መሰረት በማድረግ ልዩነት ሳይደረግ በቀን **ብር 1,300** የውሎ አበል ይከፈላል፡፡

2.4.3 የመንግሥት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በወረዳ ዋና ከተሞች ላይ ለሚደረጉ ክንውኖች አሁን በስራ ላይ ባለው የሲቪል ሰርቪስ የውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 2 እና 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በደመወዝ መጠን እና በሥራ ደረጃ ልዩነት ሳይደረግ በቀን **ብር 900** ይከፈላል፡፡

2.4.4 የመንግሥት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በሚኖሩበት ወረዳ ውስጥ በሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች በሚካሄዱ ክንውኖች ላይ ተሳትፎ ሲያደርጉ በደመወዝ መጠን ልዩነት ሳይደረግ **ብር** 250 የውሎ አበል ይከፈላል፡፡

2.4.5 በልማት አጋሮች በሚደገፉ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ክንውኖች በሚደረጉበት ከተማ የሚገኙና ከሥራ ቦታቸው ውጭ ተንቀሳቅሰው ለሚሳተፉ ተሳታፊዎች በደመወዝ መጠን እና በሥራ ደረጃ ልዩነት ሳይደረግ **ብር** 250 ይከፈላል፡፡

## 2.5 ለማህበረሰብ አባላት ተግባራዊ የሚሆን የውሎ አበል መጠን

2.5.1 የማህበረሰብ አባላት በሚኖሩበት ወረዳ ዋና ከተማ ወይም በወረዳው ውስጥ ተቀራራቢ ቀበሌዎችን በማሰባሰብ አማካይ በሆነ ቀበሌ በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ተሳትፎ ሲያደርጉ **ብር** 250 ይከፈላል፡፡

2.5.2 የማህበረሰብ አባላት ከሚኖሩበት ወረዳ ውጭ ወደ አዲስ አበባ፣ የክልሎች፣ ዞኖች እና ወረዳ ዋና ከተሞች በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ በተራ ቁጥር 2.4 ከተራ ቁጥር 2.4.1 እስከ ተራ ቁጥር 2.4.3 ድረስ በተመለከተው መሠረት ለመንግስት ሠራተኞች የሚከፈለው አበል ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 2.6 የውሎ አበል የሚከፈልባቸው ቀናት

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ሌላ የባለድርሻ አካላት ተሳታፊ ከሥራ ቦታ ውጭ በፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ክንውኖች ላይ ለተሳተፈባቸው ቀናት አሁን በስራ ላይ ባለው የሲቪል ሰርቪስ የውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 2 እና 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የደርሶ መልስ ጉዞ ቀናትን ጨምሮ የውሎ አበል የሚከፈለው ይሆናል፡፡

## 2.7 በአዘጋጆች የተሟላ አገልግሎት ሲሰጥ

ክንውኑን በሚያዘጋጀው ተቋም ወይም መ/ቤት በኩል ለተሳታፊዎች የተሟላ አገልግሎት ማለትም መኝታ፣ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት የሚቀርብ ከሆነ ተሳታፊዎች ለሚሳተፉባቸው ቀናት የውሎ አበል አይታሰብላቸውም፡፡ ሆኖም ለደርሶ መልስ የጉዞ ቀናት የውሎ አበል የሚከፈል ይሆናል፡፡

## 2.8 በደረሰኝ የሚወራረድ የመኝታ አገልግሎት

በክፍል ሁለት በተራ ቁጥር 2.4. የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የተቋማት የስራ ሀላፊዎች ለሚያደርጓቸው ክንውኖች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለቦታው ከተወሰነው የአበል ተመን ላይ የመኝታ አገልግሎት 40% በመቀነስ በአዲስ አበባ ከተማ እስከ **ብር** 2,500 ፣ በክልል እና በዞን ከተሞች እስከ

**ብር** 2,000 እና በወረዳ ከተሞች ደግሞ እስከ **ብር**1,000 ሳይበልጥ በህጋዊ ደረሰኝ የሚወራረድ የመኝታ አገልግሎት መጠቀም ይችላሉ፡፡ ለቦታው ከተወሰነው አበል ውስጥ ቀሪው 60 በመቶ የሚሆነው በጥሬ ገንዘብ የሚከፈል ይሆናል፡፡

## 2.9 የበረሃ አበል

መንግስት በረሃ ብሎ በለያቸው ቦታዎች ክንውኖች ሲደረጉ አሁን በስራ ላይ ባለው የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የበረሃ አበል ተመን መሰረት በአበሉ ላይ ተጨማሪ ሆኖ ይከፈላል፡፡

# ክፍል ሶስት

## <u>የትራንስፖርት ወጪ</u>

የሚከተሉትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ የትራንስፖርት ወጪዎች የሚወራረዱ ይሆናል፡፡

3.1. የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን እና የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ለህዝብ ማጓጓዣዎች ባወጡት የዋጋ ታሪፍ መሰረት በሚቀርብ ደረሰኝ፤

3.2. በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ፈቃድ በተሰጣቸውና የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡ ድርጅቶች የትራንስፖርት የዋጋ ታሪፍ መሰረት በሚቀርብ ደረሰኝ፤

3.3. በአየር ትራንስፖርት በሚቀርብ የደርሶ መልስ ጉዞ ደረሰኝ፤

3.4. በመስሪያ ቤት ተሽከርካሪ ለሚደረግ ጉዞ ተሽከርካሪው በአማካኝ በሊትር 5 ኪሎ ሜትር ሊጓዝ እንደሚችል ታሳቢ ተደርጎ በሚቀርብ የወቅቱ የነዳጅ ዋጋ ህጋዊ ደረሰኝ፤

3.5. በአየር ትራንስፖርት ለሚደረግ ጉዞ በመ/ቤት የትራንስፖርት አገልግሎት ካልቀረበ ከመኖሪያ ቤት/ሥራ ቦታ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ፣ ከአውሮፕላን ማረፊያ ወደ መኖሪያ ቤት/ሥራ ቦታ ለሚደረግ ለእያንዳንዱ ነጠላ ጉዞ የታክሲ ኮንትራት ወጪ መሸፈኛ **ብር** 550 የሚከፈል ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ

### 4.1 መመሪያውን ስለማሻሻል

4.1.1 ይህ መመሪያ በገንዘብ ሚኒስቴር የበላይ መሪነት በየሁለት ዓመቱ የሚከለስና የሚሻሻል ይሆናል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሁለት ዓመት በፊት ወይም ዘግይቶ ሊሻሻል ይችላል::

### 4.2 የተሻሩ መመሪዎች

ከዚህ በፊት በልማት አጋሮች ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን አስመልክቶ ሲሰራባቸው የነበሩ የውሎ አበል መመሪያዎች በሙሉ ተሽረዋል፡፡

### 4.3 መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

4.3.1 ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል::

**አህመድ ሺዴ**

**የገንዘብ ሚኒስቴር ሚንስትር**